# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከኤፕሪል 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እና ከኤፕሪል 21-30/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

## እና ምክረ ሃሳብ

ኤፕሪል 2022
አዲስ አበባ

**ርዕስ** **ገፅ**


እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ ......3

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ......5

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ......6

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ......7

ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ......7

እ.ኤ.አ እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ......8

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ......8

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ......9

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ......9

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21-30/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ ......10

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ......11

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ......12


## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት አስር ቀናት ዕረጥበት አዘል አየር ወደ ሀገራችን በመግባቱ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የደማና ሽፋን ተስተዉሏል፡፡ በተለይም ደቡባዊ የሀገሪቱ አጋማሽ ላይ አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት የተስተዋለዉ ጠንካራ የደመና ክምችት በደቡብ ኦሮሚያ ነገሌ አካባቢ ለከባድ ዝናብ መከሰት አስተዋፅ አድርጓል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የጣለዉ ከባድ ዝናብ ጎርፍ በማስከተሉ በሰዉ ህይዎትና በንብረት ላይ ጉዳት ማድረሱን የተሰበሰቡ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በአጠቃለይ ባለፉት አስር ቀናት በደቡብ፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉና ምስራቅ ኦሮሚያ፤ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በሲዳማ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብና ሰሜን ሱማሌ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸዉ ጣቢያዎች መካከል አንዳንዶቹን ለመጥቀስ ያህል በነገሌ 37.3ና 77.0፣ በአርጆ 36.4፣ በበደሌ 30.3፣ በቡሬ 30.7፣ በሞያሌ 97.7፣ በኢጃጂ 40.6፣ በሊሙ ገነት 65.5፣ በድሬዳዋ 37.8፣ በቴፒ 40.7ና 52.0፣ በሳዉላ 39.5፣ በአማን 34.6፣ በጂንካ 67.8 እና በማሻ 30.6 በሚሜ ይገኙበታል፡፡ በተጨማሪም በምዕረራብ አማራ እና ቤኒሻንጉል አካባቢዎች ላይም ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም ከአማራ ክልል በምዕራብ ጎንደር፣ በጥቂት የመካከለኛዉ ጎንደርና ምዕራብ ጎጃም፣ ከቤንሻንጉል በከማሽና አሶሳ፣ ከኦሮሚያ ክልል በሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ በኢሉ አባቦራ፣ በጅማ፣ በምዕራብና ሰሜን ሸዋ(04)፣ በደቡብ ምዕራብ ሸዋ፣ በምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ በአርሲና ምዕራብ አርሲ፣ በባሌና ምስራቅ ባሌ፣ በምዕራብ ጉጂና በጉጂ እንዲሁም በቦረና፣ በድሬዳዋና ሐረሪ፣ ከሱማሌ ክልል በኤረር፣ በኖጎብ፣ በሸበል፣ አፍዴር፣ ሊበንና ዳዋ፣ ከጋምቤላ ክልል በማዣንግ፣ በአኙዋክና ኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል በሸካ፣ በቤንች ማጂ፣ በከፋ፣ በምዕራብ ኦሞ፣ በዳዉሮ፣ በኮንታ ልዩ ወረዳ፣ በሁሉም የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ዞኖች ላይ ከ25-187 ሚሜ የሚደርስ ከ4-10 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፣ በተቀሩት የጋምቤላ፣ ቤንሻንጉል እና ሱማሌ ክልል ዞኖች እንዲሁም ከአማራ ክልል በአብዛኛዎቹ የሰሜን፣ መካከለኛዉና ደቡብ ጎንደር፣ በምስራቅ ጎጃምና ሰሜን ሸዋ(03)፣ ከኦሮሚያ ክልል በምስራቅ ሸዋ ዞኖች ላይ ከ5-25 ሚሜ የሚደርስ ዝናብ ከ4 ላነሱ ቀናት ዘንቧል (ካርታ 1 እና 2)፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በጋምቤላና በቤንሻንጉል ክልሎች ሁሉም ዞኖች፣ በመካከለኛዉና ምዕራብ ጎንደር፣ በአገዉ አዊ፣ በምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ በጥቂት የሰሜን ሸዋ(03)፣ በሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ በኢሉአባቦራና ጅማ፣ በምዕራብ አርሲ፣ በባሌ፣ በጉጂ፣ በምዕራብ ጉጂ፣ በቦረና፣ በጥቂት የምስራቅ ሐረርጌ፣ በሐረሪና ድሬዳዋ፣ በሁሉም የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እና ደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ዞኖች፣ በሲዳማ ክልል ዞኖች፣ በቆራሂ፣ በሸበል፣ በአፍዴር፣ በሊበንና ዳዋ ዞኖች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 3)፡፡


ካርታ 1   እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2   ኢ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



## እ.ኤ.አ እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የኤፕሪል ሁለተኛዉ አስር ቀናት የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በአብዛኛዎቹ የበልግ ሰብል አብቃይና የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከባለፉት አስር ቀናት በተሻለ መልኩ የተስፋፋ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተለይም በደቡባዊ የሀገሪቱ አጋማሽ አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት ከነበረዉ ጠንካራ የደመና ክምችት ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል። ይህም ሁኔታ በልግ አብቃይ አካባቢዎች ተስተውሎ የነበረውን የእርጥበት እጥረት ያሻሻለ ከመሆኑም በላይ አስቀድመው ለተዘሩ የበልግ ስብሎች እና ቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አኳያ አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በተለይም ከኤፕሪል ጀምሮ ለሚዘሩ የረጅም ጊዜ ሰብሎች ማሳን ለማዘጋጀትም ሆነ ዘር ለመዝራት ጠቀሜታው የጎላ ነበር፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የተመዘገበው ከባድ ዝናብ  በተወሰኑ ቦታዎች ለጎርፍ መከሰት አስተዋፅኦ ቢኖረውም በአዎንታዊ መልኩ ውኃን ለመሰብሰብና ለማጠራቀም ምቹ ሁኔታን የፈጠረ ነበር፡፡ እንዲሁም በቆላማ አካባቢዎች ለሚኖሩት አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደሩ አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሟላት በጎ ጎን ነበረው (ካርታ 4)፡፡


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ከ11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ አብዛኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው እና በመካከለኛው ባሮአኮቦ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ መካከለኛው አባይ፣ በጥቂት መካከለኛው እና ታችኛው አዋሽ ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ እርጥበት የተስተዋለባቸው ናቸው፡፡ በተጨማሪም አብዛኛው ተከዜ፣ የላይኛው አባይ፣ አዋሽ፣ የታችኛው ዋቢ ሸበሌ ተፋሰሶች መጠነኛ እርጥበት ሁኔታ እንደነበራቸው ተስተውሏል፡፡ የተቀሩት ተፋሰሶች ላይ በአብዛኛው ደረቅና ከፊል ደረቅ ሁኔታ አመዝኖ እንደነበር ተስተውሏል (ካርታ 5) ፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21-30/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ የበልግ ዝናብ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ በልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ እስከ ኤፕሪል የመጨረሻዎቹ አሥር ቀናት ቀጣይነት የሚኖረው ሲሆን፣ በተጨማሪም ከአመቺ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች መጠናከር ጋር ተያይዞ ወቅታዊው ዝናብ ቀስ በቀስ ወደ ምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየተስፋፋ የሚሄድበት ጊዜ ነው፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከቀን ወደ ቀን በአንፃራዊ ሁኔታ የሚጠናከሩ ሲሆን፤ በተለይም የምድር ወገብን አቋርጦ ወደ ሀገራችን እየገባ ያለዉ እርጥበት አዘል የአየር ሁኔታ የተሻለ የደመናና የዝናብ ሥርጭት በተለይም በደቡባዊ አጋማሽ፣ በመካከለኛዉና በምሰራቃዊ አካባቢዎች ላይ እንደሚኖርና በሂደትም ወደ ምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ እየተስፋፋ እንደሚሄድ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በመጠን ረገድም በአብዛኛው ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ የሚጠበቅ ሲሆን፤ አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በመነሳት በጥቂት የደቡብ ምዕራብና የደቡብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ የምዕራብና የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች፣ የምሥራቅ ሐረርጌ፣ ባሌ የምስራቅ ባሌና ጉጂና የምዕራብ ጉጂ፣ አብዛኛዉ የቦረና ዞን፤ ከሶማሌ ክልል ዳዋ፣ ሊበንና አፍዴራ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ከጋምቤላ ክልል የአኝዋክነክና መዠንግ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የአሶሳና የማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ ዞኖች፤ ሁሉም የደቡብ ምዕራብ፣ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች እንዲሁም የሲዳማ ክልል ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። በተጨማሪም ከዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች መጠናከር ጋር ተያይዞ በጥቂት ቦታዎች በተለይም በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ እና በምሥራቅ ኢትዮጵያ ላይ አልፎ አልፎ ከሚፈጠሩ ጠንካራ የደመና ክምችቶች ከባድ ዝናብ እንደሚኖር ይጠበቃል። በተጨማሪም ከአማራ ክልል የደቡብና የሰሜን ወሎ ዞኖች፣ የምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ የደቡብ ጎንደር፣ አዊ ዞኖች፣ የሰሜን ጎንደር፣ የዋግህምራ፤ ከትግራይ ክልል የምሥራቅ፣ የደቡብ ምስራቅና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ጥቂት የዞን 1፣4 እና 5 ፤ የከማሺና የአሶ ዞኖች፤ከኦሮሚያ ክልል አርሲ፣ የምዕራብ ሐረርጌ፣ የቡኖ በድሌ፣ የኦሮሚያ ልዩ ዞኖች፤ የፋፊን፣ኖጎብ፣ ጀራር ናቆራሂ ዞኖች እንዲሁም ድሬዳዋና ሀረሪ በአንዳንድ ሥፍራዎቻቸው ላይ ከመደበኛዉ ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ። በሌላ በኩል የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች በአመዛኙ ደረቃማው የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ይቆያሉ።

# እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ የኤፕሪል ወር ከመጀመሪያው አሥር ቀናት ጀምሮ የእርጥበት ሁኔታው በበልግ አብቃይ አካባቢዎች የሚሻሻልበትና ለበልግ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት የሚቻልበት ወቅት ሲሆንእንዲሁም የሚገኘው እርጥበት ለአርብቶ አደሩ አካባቢ ከፍተኛ ጠቀሜታ የሚሰጥበት ወቅት ነው፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ አካባቢዎች ጎርፍ የሚከሰትበትና እንዲሁም ለዘር በተዘጋጁና በሰብል በተሸፈኑ ማሳዎች ለይ ጉዳት ሊያስከትል የሚችልበት ወቅት ነው፡፡

በሚቀጥለው የኤፕሪል ሦስተኛው አስር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ሥፍራዎች በተለይም በደቡባዊው አጋማሽ፣ በመካከለኛውና በምሥራቃዊ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተስፋፉ እርጥበት ለመኖር አስተዋፅኦ እንደሚኖራቸውና ቀስ በቀስም ወደ ምዕራባዊ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ በመስፋፋት አንጻራዊ ጥንካሬአቸውን ይዘው ሊቀጥሉ እንደሚችሉና በመጠን ረገድም ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት እንደሚያገኙ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይህም ሁኔታ በትንበያው ላይ ለተጠቀሱት የበልግ አብቃይ እና ተጠቃሚ አካባቢዎች ለሚያከናውኑት የግብርና እንቅስቃሴ አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥር የሚጠበቅ ሲሆን፣ በተለይም ቀደም ሲል የበልግ ዝናበ ዘግይቶ በገባባቸውና የእርጥበት መቆራረጥ በነበረባቸው የአገሪቱ ክፍሎች ላይ ሰፍኖ የነበረውን የእርጥበት እጥረት በጎላ መልኩ እንደሚያሻሽለው ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም የሚጠበቀው የተለያየ መጠን ያለው እርጥበት በመካሄድ ላይ ላለው የእርሻ እንቅስቃሴ ቀደም ብለው ለተዘሩ ለበልግ ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም ከኤፕሪል ጀምሮ ለሚዘሩ የረጅም ጊዜ ሰብሎች ማሳን ለማዘጋጀትም ሆነ ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታ እንደሚኖር የሚጠበቅ በመሆኑ፣ አርሶ አደሮች ተገቢ የሆኑ ግብአቶችን በማካተት የእርሻ ሥራውን በተሟላ መልኩ ማካሄድ አስፈላጊ ነው፡፡ በአንጻሩም የሚጠበቀው እርጥበት ለአርብቶ አደሮችና ለከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለከብቶች መኖና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚኖሩ ጠንካራ የደመና ክምችቶች በተለይም በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ እና በምሥራቅ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ ሊፈጠር የሚችለው ከፍተኛ መጠን የሚኖረው እርጥበት ለወቅቱ የእርሻ እንቅሥቃሴ አመቺ ሁኔታን የሚፈጥር ቢሆንም፣ በተወሰኑ ቦታዎች ከሚኖረው ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ውሀ ገብ በሆኑና በወንዝ ዳርቻ ባሉ ማሣዎች ላይ የውሃ መጥለቅለቅንና የአፈር መታጠብን ሊያስከትል ስለሚችል ለዚሁ ችግር ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ከወዲሁ ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ

ይኖርበታል። በሌላ በኩል እርጥበት አጠር የሆኑ አካባቢዎች የሚገኘውን ውኃ የተለያየ የእርጥበት ማቆያ ዘዴዎችን አጠናክሮ በመስራት በመካከል ለሚገጥሙ ደረቅ ሰሞናት አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ማድርግ ተገቢ ነው፡፡

## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ሦስተኛው አሥር ቀናት የእርጥበት ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከቀን ወደ ቀን አንፃራዊ መጠናከር እንደሚኖራቸዉና በተለይም የምድር ወገብን አቋርጦ ወደ ሀገራችን እየገባ ያለዉ እርጥበት አዘል አየር የተሻለ የእርጥበት መጠን በደቡባዊው አጋማሽ፣ በምዕራብ፣ በመካከለኛው እንዲሁም በምሰራቃዊ ተፋሰሶች ላይ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በመሆኑም በአብዛኛው ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ ስምጥሸለቆ፣ ገናሌዳዋ፣ የመካከለኛው አባይ፣ የላይኛዉና የመካከለኛው ዋቢሸበሌ፣ አዋሽ እንዲሁም ኦጋዴን ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ እርትበት ሊኖር እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም በአብዛኛው አፋርደናከል፣ የላይኛዉና የመካከለኛው ዋቢሸበሌ፣ የላይኛዉና የመከካላኛዉ አባይ፣ የታችኛዉ አዋሽ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ተከዜ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ የእርጥበት መጠን እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም ከእርጥበት ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከመጠናከር ጋር በተያይዞ በጥቂት ተፋሰሶች ላይ በተለይም ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ ስምጥሸለቆ፣ ዋቢ ሸበሌ እንዲሁም ገናሌዳዋ ተፋሰሶች ላይ አልፎ አልፎ ሊፈጠር በሚችለው ከፍተኛ እርጥበት ምክኒያት በነዚህ ተፋሰሶች ላይ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ ቦታዎች ላይ ቅፅበታዊ ጎርፍ እና የወንዞች ሙላት ሊያሰከትል ስለሚችል ቅድመ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ የሀገሩቱ ተፋሰሶች ላይ በአመዛኙ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሆነው እንደሚቆዩ ይጠበቃል።